# <u>የግንቦት 20 ጨለማ በግንቦት 7 ብርሃን ሲገለጥ</u>

(ከአያልነሽ)

ወጣቷ ሽብሬ ደሳለኝ የ14 ዓመቱን የግንቦት 20 ጨለማ (ዘመነ ውጥረት) በደም ባህር ውስጥ ቀዝፋ ብርሃን ስታለብሰን ውድ ህይወቷን ቤዛ አድርጋልን መሆኑን ስናስታውስ ኢትዮጵያኖች ለሽብሬ ህይወት ያለን ክብርና የምንሰጠው ዋጋ ታላቅ ነው። ሽብሬ ግንቦት 20ን ዳግመኛ እንዳይመለስ በእርግጠኝነት ቀብራ፣ በደሟ ለኢትዮጵያ የብርሃን ቀንዲል መለኮሷን ደጋግማ የምታረጋግጥልን ደግሞ፣ የግንቦት 20ው ጉግማንጉግ ይበልጥ በጨለማ ውስጥ እየተደናበረ መወራጨቱን ስንመለከት ነው። የሰይጣንና የጉግማንጉግ ተምሳሌ የነበረው ግንቦት 20 በርግጥም ወደመሬት ጠልቆና ሰጥሞ መቀበሩን የሚያሳየን "የግንቦት 20 ንጉሦች" ዛሬ ግንቦት 20ና የግንቦት ወርን እንዳለፈው አሥራ አራት ዓመት ከበሮ የሚደልቁበትና የሚምነሸነሹበት ወር ሆኖ አለመገኘቱ ነው። ይልቁንም ግንቦት በጉጉት የሚጠብቁት ሳይሆን "ፀሊም ግንቦት" እንደሆነባቸው ይሰማኛል ። ለዚህም ነው ዛሬ የኢትዮጵያውያንን ዓመት በዓልና እንዲሁም ታሪካዊና የድል ቀኖቻችን ሳይቀሩ አድፍጠው በማደን ፣ ሲሻቸው የሃዘን ሳያስፈልጋቸው ደግሞ ለራሳቸውና ለአሻቸው ጉዳይ መጠቀሚያ በማድረግ ገንዘብ ሊዘርፉበት ሲቅነዘነዙ የምናያቸው። ለእነርሱ "የሠላም " ጊዜ ባሉት የ14 ዓመቱ የግንቦት 20 ጨለማ ወቅት፣ "የጠላት ሀገር የሆነችውን ኢትዮጵያ" ሀብት መዝረፍ አልቀረባቸውም ነበርና ዘረፋው ዛሬ የተጀመረና አዲስ አይደለም። የሆነ ሆኖ ግን የግንቦት 20 (ዘመነ ውጥረት) በሽብሬ ደሳለኝ (ዘመነ ሰላም) ሊተካ ባቀበቀበበት ወቅት የግንቦት 20 ጨለማ በደከመ ትንፋሹ እየተፏቀቀ የሽብሬን የብርሃን ሻማ ሊያጠፋ ሲውተረተር መመልከት ከሁሉም በላይ አስደናቂና አስገራሚ ትዕይንት ነው። ይህንን አስገራሚ ትዕይንቱን ደግሞ ቂንጣ ሚንጢ የሆኑ ነገሮችን አስቀድሞ በመርጨት የሚረጨውን መርዝ አግዝፈን እንድናየው በማድረግ አልተጎዳሁም በማለት ሲፍጨረጨር ማየታችን ነው ። በጣም የተበላና እጅ እጅ ያለ ፊዝ መሆኑን ብናውቅም የታረደ ዶሮ ነፍሱ እስኪወጣ ሲንፈራገጥ የሚረጨው ደም አካባቢውን መበከሉ አይቀሬ ነውና የሚጠበቅ ነው። በእኔ እይታ እንደታረደው/ች ዶሮ የሚንፈራገጠውን የግንቦት 20 ጨለማ ጊዜ መስጠት ማለት፣ ደሙን እየተወራጨ እንዲለቀልቀን ማድረግና ሽብሬ ህይወት ከፍላ የለኮሰችውን ውድ የግንቦት 7 ሻማ፣ እንዳሰቡትና እንደተመኙት አጥፍተው፣ ኢትዮጵያ ለዘላለም እስከ ወዲያኛው በጨለማ ወስጥ እየዳከረች እንድትኖር መፍቀድና መተባበር መስሎ ይሰማኛል።

እንዲህ ዓይነቱ የመንፈራገጥና የመላላጥ ባህሪ የማንኛውም አምባገነን ባህሪ በመሆኑ የሚያስገርም ባይሆንም የመለስ አገዛዝ ጨንቀታልና ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር እናደርገዋለን እንዳሉት "የቀድሞው መሪያችን" የወያኔ/ኢህአዴጉ ቁንጮ አቶ መለስም ቢሆንላቸውና ቢመቻቸው ከ12 ወራቶች ውስጥ ዛሬ ግንቦትን መሰረዝ ቢቻላቸው ኖሮ ከሁሉም በላይ የድላቸው ድልና ዳግመኛም እንደመወለድ በቆጠሩት ነበር። መለስ ግን ስለራሳቸው ያላቸው ግምት በ14 ዓመቱ የጨለማ ዘመን ታዝበነዋልና ለልባቸው ሲነገሩት የቆዩትን የሥልጣን ዘላለማዊነት "እንደ ቀድሞው መሪ" በአደባባይ ላይ መለፈፍ አላስፈለጋቸውም።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ ! በጽሁፌ ላይ አቶ መለስን "አንቱ" እያልኩ ስጠራ በቅድሚያ ለምወዳት ሀገሬ ለኢትዮጵያ፣ ለናንተ ለተከበራችሁ አንባቢዎቻና ሁሌም ለማደንቀውና ለማከበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ባለኝ ታላቅ አክብሮት እንደሆነ ትገንዘቡልኝ ዘንድ ስጠይቅ በታላቅ ትህትና ከአክብሮት ጋር ነው።

ግንቦት 7 ህዝባችን በድምጹ ያሻውን የመረጠበትና ታሪኩን የጻፈበት፣ የአቶ መለስ አገዛዝን (ዘመነ ውጥረት) ደግሞ አከርካሪውን የመታበትና ያሽመደመደበት በመሆኑ፣ ይህንን ድል ጠብቀን ለመቀጠልና የህዝባችንን ድምጽ ለማስከበር ህዝባችን እንዳደረገው በእኛ በኩልም ማድረግ ያለብን፣

አሁንም ኢላማውን ያወቀ፣ የተባበረ፣ የተቀናጀና  በግንቦት 20 (ዘመነ ውጥረት) ላይ ብቻ ያነጣጠረ እንቅስቃሴ ማድረግ የግድ ይለናል። የመለስ አገዛዝ ፈለግነውም አልፈለግነው በግንቦት 7 የህዝብ ምርጫ በእጅጉ መቁሰሉን ስለተረዳና የደረሰበት መብረቅም ከባድ በመሆኑ ሊያገግም አለመቻሉን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የመብረቁ ጨረር የአገዛዙን የውስጥ አካል ሁሉ ሰርስሮ ክፉኛ በመጉዳቱ ምንም ዓይነት መድኃኒት ቢታዘዝ ለጊዜው የህመም ስሜቱን ያስታግስ እንደሆን እንጅ ለወዲያኛው ፈውስ እንደማይሰጥ ግን አዋቂን አይጠይቅም። አቶ መለስና አገዛዛቸው አሁን በሚያዳምጡት ልባቸው የሚያዙትና የሚወስዱት መድሃኒት፣ ራሳቸው ለልባቸው እንደሚነግሩት ለማገገም እንዳልሆነ ስለሚያውቁት ነፍስ ናትና ነፍስ እስክትወጣ ለነፍስ ማቆያ የሚወስድ ማናቸውም መድሃኒት፣ ከአቶ መለስ ሌላ ዛሬ፣ እንኳንስ ከእኛ ‘’ከእመቤት’’ አዜብ ጎላ እጅ ቢሰጥ እንክብሉን አምነው እንደማይወስዱ ለማንም ግልጽ ነው። ስለዚህ የማይድንን ቁስለኛና በሽተኛ (እንደማይድንና እንደማያገግም እየታወቀ) ጥቂቶች በዙሪያው በመኮልኮልና በማጨፈር የደከመን ነፍስ ከአቅሙ በላይ እንዲተንፍስና ብርቱ ነፍስ ያለው ለማስመሰል ጫማ ሲጨርሱ ማየት፣ ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ስም ከማትረፍ በቀር ትርፍ የሌለው ኪሳራ ነው።  ታዲያ ለምን ! እሳት ይዞ ከእሳቱ ጋር ሌላ  ይዞ እንዲሞት ከማድረግ፣ ልናድነው የሚገባን አገርና ህዝብ እየጠበቀን ነውና ፊታችንን እሳት ወደሚበላው ህዝብና ሀገር እንድናዞር ስጠይቅ፣ ብዙ ጊዜዎቻችንን፣ ጉልበታችንን፣ ቅንጅታችንና ህብረታችንን ለኢትዮጵያና ለህዝባችን በበቂ እንዳላዋልን ስለሚሰማኝ ነው ። በእርግጥ የሚደረጉና የተደረጉ የትብብርና የጋራ ሥራዎች አነሰም በዛ ውጤት እንዳላቸውና በተነጣጠረበት ኃይል ቁስል ላይ ቁስሉን በየጊዜው ማድማታቸውንናንና ማባባሳቸውን፣ አሌ ማለት አይቻልም። ይበልጥ ግን በብዙ ጎኑ የጥቃት ምት የደረሰበትን ጠላት ላይድን ከምናፈራግጠው ሁላችንም በአንድ ላይ፤ ያሉብንን የውስጥ ጣጣ ፈንጣጣና አንጃግራንጃ ወደጎን ትተን፣ በዋናውና ፊታችን ላይ ተደቅኖ በምናየው፣ አገራችንንም ይዞ ሊጠፋ በሚያጣጥረው ጠላታችን ላይ ኃይላችንን አስተባብረን መረባረብ፣ ለነገ የማይሉት እነሆኝ ብሎ የቀረበልን የሀገራችን ኢትዮጵያ  አገር አድን ጥሪ ነው። ይህንን የሀገር አድን ጥሪ ምንም ዓይነት አጥር ሳናበጅ፣ በተባበረና በተቀናጀ መንገድ ኢትዮጵያን ለማጥፋት በሚያጣጥረው ጠላቷ ላይ ማዋል ከቻልን፣ ኢትዮጵያን የማዳንና ሃገራችንን የማቆየቱ ታላቅ ተልዕኮ በቅድሚያ ተገባደደ ማለት ይቻላል።  በእኔ በኩል እያንዳንዳችን የምናይበት ዕይታ ርቀትና ጥልቀት ይለያይ ይሆናል እንጅ በበርካታ ጉዳዮች ዙሪያ ፣ ታስቦም ሆነ ሳይተሰበ፣ ተቀናጅተውና ተቀናበብረው የተደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ለውጤት ሲበቁ ተመልክተናል። በቅርቡ እንኳን ምሳሌ የሚሆነን የግንቦት 20 ጨለማዎች ‘’ሚሌኒየም’’ ብለው መጀመሪያ በጨኹበት ላንቃቸው ዛሬ በዚያው ልክ መጮህ አልተቻላቸውም ። ለዚህም ነው በየጊዜው አገዛዙ የሚያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች በጥሞና ለሚከታተል ሰው ላይ ላዩን እንድምናየው ሳይሆን፣ በጥልቀት ላስተዋለው የአገዛዙ አካሄድ በደመ ነፍስ የሚወራጭ መሆኑን ማየት የሚሳን የማይሆነው።  አንዳንዴም እኮ አገዛዙ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በሙሉ በዕቅድ እየወጡ የሚደረጉና የሚፈፀሙ ሳይሆኑ ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ጭምር ሊደረጉ እንደሚችሉ መዘንጋት አይገባም።  ቢጤአቸው የሆኑትን መንግሥቱ ኃ/ማርያም የተኩት አቶ መለስ ራሳቸው እንደሚያውቁት፣ ጠራቸውን ‘’በዘመቻ ቢሊሱማ’’ አምቦ አስገብተው እያለ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ቱባ ቱባ ባለሥልጣኖች ምንም ነገር እንደሌለ ለማስመሰል አዲስ አበባ ተቀምጠው በእምነበረድ ቤት ያሰሩ እንደነበር አይዘነጋም። ‘’በዘመቻ ዋለልኝና በዘመቻ ቴዎድሮስ ስም’’ ወሎ፣ ጎጃምና ጎንደር እየገሰገሰገሱ ወደ አዲስ አበባ  ልዘልቅ ነኝ በማለት አቶ መለስ ለመንግስቱ ኃ/ማርያም ቡታ እየላኩ፣ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ልዑክ በለንደን ለድርድር ተቀምጠ እንደነበር ይታወሳል። አስቂኝ ትውስታ ! ስለዚህ በመለስና በአገዛዛቸው በኩል ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ የሚደረጉና የሚወስዱ እርምጃዎች ሁሉ ሁልጊዜ በዕቅድና በተረጋጋ ሁኔታ ላይ የሚደረጉና የሚሰሩ እንዳልሆኑና በተጨማሪም እንደጠላት ለምንቆጠረው ኢትዮጵያኖች ብቻ፣  የሚደረግ እንቅስቃሴ ሳይሆን አብረው ለመሞትና እንዲሞቱም ደሞዝ የሚከፈላቸውና የሚበሉ በቂ ካድሬዎች ስላሉ፣ በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ ለመምታት ታስቦም የሚደረግ ያልሞት ባይ ተጋዳይ የዶሮዋ ዓይነት መንፈራገጥ ጭምር ነው። ስለዚህ ሁላችንም በግንቦት 20ው(ዘመነ ውጥረት) ላይ በደንብ ብናተኩርና ብንመለከት አካሄዱ የእውር ድንብስ ጉዞ መሆኑን ለመረዳት የማያዳግተና  የማይሳን የቀን ብርሃን ነው።

ለነገሬ መነሻ አድርጌ የተነሳሁበት አብይ ጉዳይ የግንቦቱን ድል ለማስመለስ የምናደርገው ትግል ዋናና ቁልፍ በመሆኑ ከምንም በላይ ለኢትዮጵያችን ውስብስብ ችግር መፍቻና ማሰሪያ የሆነውን ብቸኛ የግንቦት 7 የህዝብ ቁልፍ ፣ ህዝባችን ለገደለውና በጣር ላይ ላላው አገዛዝ ነፍስ ማቆያ መተው፣ ጉዳቱ ከኢትዮጵያ አንፃር ከባድ መሆኑን ሁላችን በጥሞና እንድንገነዘበው ለማሳሰብ ነው። ይህንን ድል ለማስመለስና የህዝህባችንን ድምጽ ለማስከበር የምናደርገው ትግል ሳናቋርጥ በተቀናጀና በተባበረ <u>የህብረት ክንድ</u> መቀጠል ያለበት በሶስት ዋና ዋና መሰረታዊ ምክንያቶች ነው።

ሀ) የግንቦት 7 ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በዓለም ህዝብ ፊት ያለምንም ችግር መብቱን ተጠቅሞ ድምጹን በመስጠት የፈለገውንና ያሻውን የመረጠበት፣ ራሱ ወያኔም « እንከን የለሽ » በማለት ያረጋገጠውና አገዛዙ የመረጣቸው የዓለም ታዝቢዎች በሙሉ በአብዛኛው የተቀበሉት የምርጫ ሂደት በመሆኑ፥

ለ) ህዝባችን ይህንን ዕድል ከመምረጥ ጀምሮ ድምጹ እንዳይሰረቅበት እስከመከላከል ድረስ ተጠቅሞ የሞት-ሽረት ተጋድሎ ያደረገበትና ህይወት የከፈለበት በመሆኑ፥

ሐ) የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ይህንን የተሸነፈበትን ምርጫ ህዝብ ያሸነፈበት ምርጫ ሳይሆን በተቃዋሚዎችና ወያኔ እንደሚለውም ተቃዋሚዎች በፈጠሩት ''ግርግር'' ምክንያት የምርጫ ሂደቱም ሆነ የድምጽ ቆጠራው ውጤት መደናቀፉንና ማቆሙን በመግለጽ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ ውጭ አድርጎ፣ እራሱ የፈጠረውን የተድበሰበሰ ታሪክ እንደታሪክ እንዲቀመጥ በመፈለግና ሥልጣኑን ከለቀቀም በኋላ (መለቀቁ ስለማይቀር) ያድበሰበሰውን ታሪክ ታሪክ ሆኖ እንዲቀጥል ስለሚፈልግ ነው።

የወያኔ/ኢህአዴግ አገዝዝ ደግሞ የሌለ ታሪክ በመፍጠር ባለ 100 ዓመት ታሪክ አከናንቦናልና የሌለ የተረት ታሪክ ፈጠሮ ታሪካችሁ የማለት ባላባት ነው።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ! ኢትዮጵያን ወያኔ/ኢህአዴግ ሊያስትዳድር ብቃትና ችሎታ ያልነበረውና የሌለው እንደነበር በድምጹ የነገረውንና ያወረደውን ሕገወጥ የመለስ አገዛዝ፣ ላይድንና ላይተርፍ ነገር እድሜ በመስጠት፤ የህዝባችንን አደራ በልተን ብንገኝ የኢትዮጵያን ጣር ማባባስ እንጅ ፈውስ ሊሆናት እንደማይችል ተገንዝበን፣ ሙሉ ህብረታችንንና ቅንጅታችንን ዛሬም ለህዝባችንና ለሀገራችን ኢትዮጵያ እንድናውል በድጋሚ ከታላቅ አክብሮት ጋር በትህትና እጠይቃለሁ።

ለሀገራችን የሚበጃትን መድኃኒት የምንሰራው፣ የምንቀምመውና የምንመጥነው እኛው ራሳችን በራሳችን እንጅ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ዛሬም ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ በድጋሚ እየተነገረን ይመስለኛል። በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ ተጠልፈው በነበሩት የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ቱሪስቶች ላይ መንግሥቶቻቸው ዜጎቻቸውን ለማስፈታትና ሁኔታውም እንዲጣራ የመለስን አገዛዝ ወጥረው መያዛቸውን በዓለም የዜና ማሰራጫዎች ተከታትለናል። ባዕዳኖች ዜጎቻቸውን አስይዘው ቁጭ ብለው መብላትና ማየት አይቻላቸውምና እስከመጨረሻው ሄደው ለጉዳዩ እልባት ማስገኘት ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ጉድይ እንደእኛ በቸልታና በሆነና ባልሆነ ሰበብ ጊዜ በመውሰድ ቢራዘም የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ህዝብ መንግሥቶቻቸውን አስጨንቀውና ወጥረው በመያዝ ዜጎቻቸውን የማስለቀቅ ኃይል አላቸው። (ይህ አንዳንዶች እንደሚሉት ለባዕዳኖች/ፈረንጆች ብቻ የተሰጠ ፀጋ አድርገው እንደሚቆጥሩት አድርገን ካላየነው በቀር) ይህ የሚያመላክተን ዛሬም ለራሳችን ጣጣ መጀመሪያ ራሳችን በአንድ ላይ ቆመን የራሳችንን ቤት ካላሳመርን ባዕዳኖች ለራሳቸው ጥቅም ካልሆነ ከጉዳይ እንደማይቆጥሩን ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለእዳ እንደማይቀበለው የሀገራችን ብሂል ደጋግሞ ይነግረናል። ለራሳችን ጉዳይ ራሳችን በትጋት ተባብረንና ተቀናጅተን የኃይላችንን ብርታትና ልክ በህብረት ካልሰየን፣ የታሰሩ ዜጎቻችንን ሆነ ልትጠፋ በመንጠራወዝ ላይ ያለችውን ሀገራችንን ለማዳንና ለመታደግ ፈጽሞ አይቻልምና።
ለዚህ ጽሁፌ ማሳረጊያ ትሆነኝ ዘንድ የጋሼ ኃይሉ ገ/ዮሐንስ (ገሞራው) ከተወዳጇና ከማታረጀው በረከቱ

እንዲ የሆነችው «በረከተ መርገም የግጥም ጥራዙ ውስጥ» የማርከችኝን የግጥም ስንኝ በማቅረብ እሰናበታለሁ።
(በቅድሚያ ጋሼ ኃይሉ ገ/ዮሐንስ (ገሞራውን) ፈቃድ ሳልጠይቅ «ከበረከተ መርገም የግጥም ጥራዙ» ውስጥ አንዷን የግጥም ስንኝ በመጠቀሜ ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ።) በሌላ በኩል የተዋስኳት የግጥም ቋጠሮ የጽሁፌን ይዘትና መልዕክት ቁልጭ አድርጋ ስለምትገልፅልኝ ደግሞ ጋሼ ኃይሉን በጣም አመሰግናለሁ።
የመረጥኳት የግጥም ስንኝ እነሆ !

ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎህ ሲከሸፍ፥
ሁኔታው ሲጠጥር፣
ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር።

በማለት ህዝባችን በአንድ ላይ ቆሞ በህብረትና በተቀናጀ ኃይል የሰጠንን ድልና የህብረት ክንድ ባልባሌና መናኛ በሆኑ ነገሮች ላይ በማባከን በማዋል ክንዳችንን እናዝለው አላለሁ !

የህዝባችን ድምጽ ይከበር !
የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ !
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !